# ቴክሳስ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ የኢሕአፓ ዓባላት በዳላስ ከተማ ተሰበሰቡ

ባለፈው ቅዳሜ ሚያዚያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም (May 5, 2012) ከቴክሳስ የተለያዩ ከተሞች የመጡ የኢሕአፓ ዓባላት አጠቃላይ ስብሰባ አድርገዋል። ስብሰባው የተካሄደው በዳላስ ከተማ ሲሆን ዓባላት በአገራቸውና በድርጅታቸው ዙሪያ አንገብጋቢ በሆኑ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይትን አድርገዋል። አገሪቱ የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ በስፋት የገመገሙ ሲሆን በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓትን እውን ለማድረግ እየተካሄደ ያለውን ሕዝባዊ ትግል ለማጎልበት የድርጅታቸው መጠናከር ወሳኝ መሆኑን አምነው ለዚህ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ለሚጠይቅ ተግባር ዝግጁነታቸውን ከመረመሩ በኋላ በከፍተኛ የመነሳሳት ስሜት አስረግጠው በተለይም በአሁኑ ሰዓት አገሪቱ ውስጥ በፍጥነት እየገፋ የመጣውን ሕዝባዊ መነሳሳት ከፍተኛ ግምት በመስጠት መሰል ስብሰባዎች በተቀራራቢ ጊዜያት ማደረግ እንዳለባቸው አፅንዖት ሰጥተው ስብሰባቸውን ደምድመዋል።